**ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ**

# የ2024 በጀት አመት (FY24) የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ

## የቅጥር ሂደት ለውጥ በልጅ እድገት ተቋም (CDF) የደመወዝ ክፍያ ቀመር ሽልማቶች ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድር

በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ የ2024 የበጀት አመት (FY24) ላይ የሚሳተፉ የልጅ እድገት ተቋማት በኦፊስ ኦፍ ዚ ስቴት ሱፐርኢንተንደንት ኦፍ ኤጁኬሽን የወጡትን ዝቅተኛ ደሞዞች የሚያሟሉ ወይም የሚበልጡ ደመወዞችን ለሁሉንም ብቁ መሪ አስተማሪዎች እና ረዳት አስተማሪዎች[1] መክፈል አለባቸው፡፡

### ለተሳታፊ ተቋማት የቅድመ ልጅነት ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ዝቅተኛ ደመወዞችን የሚመለከት ቁልፍ መረጃ

ብቁ ለሆነ የቅድመ ትምህርት አስተማሪ ዝቅተኛው የደመወዝ መስፈርት በሰራተኛው የስራ መደብ እና በቅድመ ትምህርት ፈቃድ ሰጭ መሳሪያ ክፍል (DELLT) በተመዘገበው፣ በተገመገመው እና በጸደቀው ከፍተኛ የትምህርት ማስረጃ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ተሳታፊ ተቋማት (የጸደቀ መልቀቂያ ካገኙት ውጪ) የመጀመሪያውን የሩብ አመት የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት ከተቀበሉ በኋላ ለሁሉም ብቁ ሰራተኞች ዝቅተኛውን የደመወዝ መስፈርቶች እንዲያሟሉ ይጠየቃሉ፡፡ የገንዘብ ድጋፎችን ከመቀበላቸው በፊት ዝቅተኛውን የደመወዝ መስፈርቶችን ለማሟላት ወይም ከዚያ ለመብለጥ አቅም ያላቸው ተቋማት በገንዘብ ድጋፍ አቅርቦት ላይ በመመስረት እንዲህ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

**አንድ ጊዜ አንድ ተቋም የመጀመሪያውን የCDF ደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማቱን ከተቀበለ በኋላ፣ ሰራተኛው የተቀጠረበት ቀን መቼም ቢሆን፣ ተቋሙ በፕሮግራሙ ውስጥ ተሳትፎ ለሚቆይበት ጊዜ፣ ብቁ በሆኑባችው የስራ መደቦች ለተቀጠሩ ለሁሉም ብቁ ሰራተኞች ዝቅተኛ ደመወዞችን የሚያሟሉ ወይም የሚበልጡ ደመወዞችን መክፈል አለበት፡፡ ተቋሙ የጸደቀ መልቀቂያ ከሌለው በስተቀር አዲስ የተቀጠሩ መሪ አስተማሪዎች እና ረዳት አስተማሪዎች ዝቅተኛ የደመወዝ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ወይም ከዚያ የሚበልጡ ደመወዞች ወይም የሰአት ክፍያዎች ሊከፈሏቸው ይገባል፡፡**

### ለተቋማት የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመርን የሚመለከት ቁልፍ መረጃ

**Table 1.**

| የDELLT መዝገቦችን ለማዘመን የFY24 ቀነ-ገደቦች | | |
|---|---|---|
| **ሩብ ዓመት** | **ቀነ-ገደብ** | **የሽልማት ክፍያ** |
| ሩብ አመት አንድ | ኖቬምበር 6፣ 2023 | ዲሴምበር |
| ሩብ አመት ሁለት | ጃኗሪ 31፣ 2024 | ማርች |
| ሩብ አመት ሶስት | ኤፕሪል 30፣ 2024 | ጁን |
| ሩብ አመት አራት | ጁላይ 31፣ 2024 | ሴፕቴምበር |

በFY24 የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ መርጠው የገቡ ተቋማት የCDF ደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመርን በመጠቀም የሩብ አመት ክፍያዎችን ያገኛሉ፡፡ መዝገቦች የዘመኑ፣ ትክክለኛ እና ሁሉንም የተጠየቁ ደጋፊ ሰነዶች ማካተታቸውን ለማረጋገጥ ተሳታፊ አቅራቢዎች በOSSE በወጡት የሩብ አመት ቀነ ገደቦች በDELLT ውስጥ ያሉትን የሰራተኞች መዝገቦች መገምገም እና ማዘመን አለባቸው (ሰንጠረዥ1 ይመልከቱ)፡፡ ይህ የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማቶች ትክክለኛ መሆናቸውን ያረጋገጣል፡፡ እነዚህ ቀነ ገደቦች የወጡት ተቋማት ተዛማጅ ለሆኑ የሰራተኞች መዝገቦች ደጋፊ ሰነዶችን እንዲያዘምኑ እና እንዲጭኑ ነው፡፡ እያንዳንዱን የሩብ አመት ቀነ ገደብ ተከትሎ፣ የፈቃድ ሰጭ ልዩ ባለሙያዎች የአንድን ተቋም የሩብ አመት ክፍያ ከማስላታቸው በፊት አዲስ የተጫነውን ሰነድ ለማጽደቅ የሚገመግሙ ይሆናል፡፡ የፈቃድ ሰጪ ልዩ ባለሙያው ጥያቄዎች ካሉት ወይም ተጨማሪ ሰነዶች ከፈለገ፣ ተቋሙ የሚያስታውቅ ይሆናል፡፡ በሰራተኞች እና/ወይም በድጎማ ምዝገባ ላይ የተደረጉ ለውጦች የሽልማት መጠኖች ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የቅጥር ሂደት ለውጦችን እና/ወይም የድጎማ ምዝገባን ለመግለጽ በDELLT ውስጥ ያሉ የሰራተኞች መዝገቦችን ማዘመኛ ቀነ ገደብ ካለፈ በኋላ ሽልማቶች በሩብ አመቱ እንደገና ይሰላሉ፡፡

**OSSE በሩብ አመት ክፍያዎች መካከል በሚደረጉ ለውጦች ላይ በመመስረት ለCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ክፍያዎች ወደ ኋላ የሚሰሩ ማስተካከያዎችን አያደርግም (የሚከተሉትን ጨምሮ ነገር ግን በእነዚህ ሳይወሰን፡- በመሪ መምህራን እና ረዳት መምህራን ብዛት ላይ የሚኖሩ ለውጦች፣ በሰራተኞች የተያዙ የትምህርት ማስረጃዎች ላይ የሚኖሩ ለውጦች ወይም በድጎማ ምዝገባ ላይ የሚደረጉ ለውጦች)፡፡ ተቋሙ በሩብ አመቱ የሰራተኛ መልቀቅ ወይም የድጎማ ምዝገባ መቀነስ ካጋጠመውOSSE ተቋማት የሽልማት የገንዘብ ድጋፎችን እንዲመልሱ አይጠብቅም፡፡ በOSSE ከወጡት ቀነገደቦች ጀምሮ በተቋሙ የDELLT መዝገቦች ውስጥ ውስጥ የገቡ የተቋሙ የቅጥር ሂደቶች ላይ የተደረጉ ማንኛቸውም ለውጦች (አዲስ ተቀጣሪዎችን፣ መልቀቅ እና ለነባር ሰራተኞች በሰራተኞች አይነቶች ወይም በስራ መደቦች ላይ የተደረጉ ለውጦችን ጨምሮ) በሚቀጥለው የሩብ አመት ሽልማት ስሌት ላይ የሚገለጹ ይሆናል፡፡**

---

1 ለቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ዓላማዎች፣ የ DC ኮድ §4-401 “መምህር” እና “ረዳት መምህር”ን በOSSE የፈቃድ አሰጣጥ ደንቦች ላይ ከተገለጹት በላይ በሰፊው ይገልፃል፡፡ ለቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ “መምህር” በልጅ እድገት ማዕከል ውስጥ ያለ መምህርን፣ የሞንቴሶሪ መምህርን እና የቤት ውስጥ ወይም የተስፋፋ የቤት ውስጥ የልጅ እንክብካቤ አቅራቢን ያካትታል፡፡ “ረዳት መምህር” በልጆች ልማት ማእከል ውስጥ ረዳት መምህር እና በህፃናት ማሳደጊያ ቤት ውስጥ ተባባሪ ተንከባካቢን ያካትታል፡፡

የቅጥር ሂደት መለዋወጦች ያጋጠሟቸው ተቋማት የወደፊት ግዴታዎችን ለመሸፈን ማናቸውንም ትርፍ የገንዘብ ድጋፎች ሊሆን በሚችል መልኩ መያዝን ጨምሮ ብቁ ለሆኑ ሰራተኞች ዝቅተኛ ደመወዞችን እንዲከፍሉ ለማስቻል በሁሉም ሩብ አመታት ከቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ የሚያገኙትን የገንዘብ ድጋፎች ማስተዳደር ይጠበቅባቸዋል።

የሰራተኞች ለውጦች የተቋሙ ሃላፊነቶች እና የሽልማት ስሌት ላይ ምን ያህል ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ለማግኘት በሰንጠረዥ 2 ላይ ያሉትን ገለጻዎች ከዚህ በታች ይመልከቱ፦

**ሰንጠረዥ 2.**

| **የሰራተኞች ለውጥ ገለጻዎች ናሙና** | | |
|---|---|---|
| **ገለጻ** | **የተቋም ሃላፊነት** | **የCDF የደመወዝ ክፍያ የገንዘብ ድጋፍ ቀመር ሽልማት** |
| አንድ ብቁ የሆነ ሰራተኛ ተቋሙን ለቆ ይወጣል… | ተቋሙ የሰራተኛውን መልቀቅ ለመግለጽ በDELLT ውስጥ ያለውን የሰራተኞች መዝገብ ማዘመን አለበት (ለምሳሌ፦ በሰራተኞች መዝገብ ላይ የተለየበትን ቀን አክሏል፣ እንዲሁም በDELLT ላይ የተጫኑትን የቅጥር/የመለያ ቅጾች አዘምኗል)<br>ተቋሙ የገንዘብ ድጋፎችን ለOSSE መመለስ አይጠበቅበትም። | OSSE በDELLT ላይ እንደተገለጸው የቅጥር ሂደት ለውጥን ለማሳየት በቀጣዩ ሩብ አመት የተቋሙን ሽልማት የሚያስተካክል ይሆናል። |
| አዲስ ብቁ የሆነ ሰራተኛ ተቀጥሯል… | ተቋሙ ሁሉንም የተጠየቁ ደጋፊ ሰነዶች ጨምሮ አዲሱን ቅጥር ለመግለጽ በDELLT ውስጥ አዲስ የሰራተኛ መዝገብ መፍጠር አለበት።<br>ተቋሙ በDELLT OSSE የሰራተኞችን መዝገብ ማጽደቁን ተከትሎ ለሰራተኛው አዲሱን ዝቅተኛ ደመወዝ መክፈል መጀመር ይኖርበታል። | OSSE በDELLT ላይ እንደተገለጸው የቅጥር ሂደት ለውጥን ለማሳየት በቀጣዩ ሩብ አመት የተቋሙን ሽልማት የሚያስተካክል ይሆናል። |
| ብቁ የሆነ ሰራተኛ ከፍተኛ የትምህርት ማስረጃ ወይም ዲግሪ አገኘ (ለምሳሌ፦ በቅድመ ልጅነት ትምህርት ተባባሪ ዲግሪ ያለው መምህር በቅድመ ልጅነት ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪውን ጨረሰ)… | ተቋሙ የአዲሱን ሰራተኛ የትምህርት ማስረጃ በደጋፊ ሰነዶች ለማሳየት በDELLT ውስጥ ያለውን የሰራተኛ መዝገብ ማዘመን አለበት።<br>ተቋሙ በDELLT OSSE የሰራተኞችን መዝገብ ማጽደቁን ተከትሎ ለሰራተኛው አዲሱን ዝቅተኛ ደመወዝ መክፈል መጀመር ይኖርበታል። የጸደቁ የሰራተኞች መዝገቦች "ጸድቋል" የሚሉ ይሆናል ወይም ባዶ ሁኔታ ይኖራቸዋል። | OSSE በDELLT ላይ እንደተገለጸው የቅጥር ሂደት ለውጥን ለማሳየት በቀጣዩ ሩብ አመት የተቋሙን ሽልማት የሚያስተካክል ይሆናል። |
| አንደ ብቁ ሰራተኛ በአዲስ የሰራተኛ አይነት (ለምሳሌ ከረዳት መምህርነት ወደ መሪ መምህር) ተመደበ… | ተቋሙ አዲሱን የሰራተኛ አይነት በደጋፊ ሰነዶች ለማሳየት በDELLT ውስጥ ያሉትን የሰራተኞች መዝገቦች ማዘመን አለበት።<br>ተቋሙ በDELLT OSSE የሰራተኞችን መዝገብ ማጽደቁን ተከትሎ ለሰራተኛው አዲሱን ዝቅተኛ ደመወዝ መክፈል መጀመር ይኖርበታል። | OSSE በDELLT ላይ እንደተገለጸው የቅጥር ሂደት ለውጥን ለማሳየት በቀጣዩ ሩብ አመት የተቋሙን ሽልማት የሚያስተካክል ይሆናል። |
| አንድ ብቁ የሆነ ሰራተኛ በጊዜያዊ ፈቃድ ተሰቶታል፣ ለምሳሌ የሚከፈልበት የቤተሰብ ፈቃድ… | ተቋሙ በፈቃዱ ጊዜው ወቅት በDELLT ውስጥ የሰራተኞች መዝገቦችን ሊይዝ ይገባል እንዲሁም ሰራተኛው ጊዜያዊ ፈቃድ ላይ መሆኑን የሚያመለክት ትክክለኛ ሰነድ በተቋሙ ፋይል ላይ መያዝ አለበት።<br>ተቋሙ ከፈቃድ ፕሮግራሞች ጋር የተያያዙ ሁሉንም ህጎች ሊከተል ይገባል፣ ለምሳሌ ቤተሰብ እና የህክምና ፈቃድ ህግ እና የዲሲ የሚከፈልበት የቤተሰብ ፈቃድ።<br>ተቋሙ በማይከፈልበት የፈቃድ ጊዜ ለሰራተኛው መክፈል አይጠበቅበትም።<br>ተቋሙ የገንዘብ ድጋፎችን ለOSSE መመለስ አይጠበቅበትም። | በተቋሙ ሽልማት ላይ ምንም አይነት ለውጥ አይኖርም። |

ከሰራተኞች ለውጦች እና ከቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃው የገንዘብ ድጋፍ ክፍያ ጋር ለተያያዙ ጥያቄዎች፣ እባክዎ ለOSSE.ECEPayEquity@dc.gov ኢሜይል ይላኩ።